በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት
ኮሚሽን

# በከተማ ግብርና ከለውጡ በኋላ በተሰሩ ስራዎች የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች







ታህሳስ 2018 ዓ.ም
አዲስ አበባ፤ኢትዮጲያ







# The Management





ዋና ኮሚሽነር
አቶ ባዩ ሽጉጤ



የአስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ
አቶ ጌታሁን አበበ



ም/ኮሚሽነር ሰርተፍኬሽን
እንስፔክሽን እና ሬጉላቶሪ
ዘርፍ
ጸጋ ለማ (ዶ/ር)



ም/ኮሚሽነር አርሶ አደር
ማቋቋም ልማት ዘርፍ
ወ/ሮ ሉሉ ዳለቻ



ም/ኮሚሽነር ከተማ ግብርና
ዘርፍ
አቶ መሀመድ ሊጋኒ



የእንስሳት ልማት እና
ለኅቀት ማእከል ኃላፊ
አቶ አሌክስ ደመቀ



በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና
ልማት ኮሚሽን
ዋና ኮሚሽነር አቶ ባዩ ሽጉጤ

## የዋና ኮሚሽነር መልዕክት

ሀገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት የለውጥ ዓመታት በተለያዩ የልማት መስኮች አመርቂ የተባሉ ኢኮኖሚያዊ እድገትና ማህበራዊ ለውጥ አስመዝግባለች፤ ሚሊዮኖችን ከአስከፊ ድህነት ለማውጣት ተችሏል።

ከተማችን አዲስ አበባም ለውጡን መሰረት አድርጋ ሰፋፊ ሰው ተኮር ፕሮጀክቶችን እና የልማት ሥራዎችን በመስራት የብዙዎችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመፍታት ችላለች።

የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽንም በከተማ አስተዳደሩ ስር ሰዶ የቆየውን የአርሶ አደሮች በይዞታቸው ላይ የማልማት ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ፣ በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የለቀቁ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸው በአግባቡ መልሰው እንዲቋቋሙና እንዲለሙ፣ የከተማ የግብርና ልማት እንዲስፋፋና እንዲዘምን፣ የእንስሳት ጤና ጥበቃ እንዲሻሻል፣ የሬጉላቶሪና የዝርያ ማሻሻል አገልግሎት እንዲዘምን፣ የግብርና ምርት ውጤቶች አቅርቦት እንዲሻሻል እና የኑሮ ውድነት እንዲረጋጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆኖ ልዩ ትኩረት በመስጠት እየሰራ ይገኛል። ሌላው የከተማዋ ነዋሪዎች በጓሮ አትክልት ልማት እና በ“የሌማት ትሩፋት” (በእንስሳት እርባታ ዘርፍ) ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ በከፍተኛ ሁኔታ እየሰራ ይገኛል።

“በሌማት ትሩፋት” ፕሮግራም የከተማችንን ሌማት ‘በወተት ተዋጽኦ፣ በዶሮ፣ በማር፣ በጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ምርት ማትረፍረፍ ለነገ የማይባል ሥራችን ነው።

ይህ ከሆነ ደግሞ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ይቻላል። ሥጋ፣ እንቁላል፣ ማር፣ ወተት እና የወተት ተዋጽኦዎች የቅንጦት ምግቦች ሳይሆኑ አስፈላጊ የሥርዓተ ምግብ አቅርቦቶች ሆነው የዕለት ከዕለት ማዕዳችን ላይ የሚገኙ ይሆናሉ። እየሆኑም ነው።

እስካሁን ባለን እንቅስቃሴ መልካም የሚባል ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል። በዚህ ሂደትም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ከፍጆታ ባሻገር የከተማ ግብርና ምርትና ምርታማነት ማዕከል እየሆኑ ይገኛሉ።

የከተማ ግብርና ለከተማችን ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያለው በመሆኑ ከተማ አስተዳደሩ ልዩ ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እያደረገ ይገኛል። ለከተማ ግብርና መስፋፋትና መጠናከር የማይተካ ሚና ያላቸው ግብዓቶች እንደ የውሃ፣ የእንስሳት መኖ፣ ምርጥ ዘር፣ የተሻሻሉ የወተት ላም ዝርያዎች፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት እንዲሻሻል እና የማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲጎለብት ጠንክረን የምንሰራባቸው ስራዎች ይሆናሉ።

ውድ የግብርና ቤተሰቦች የከተማ ግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ የበኩላችሁን የማይተካ አስተዋጽኦ እንድታበረክቱ ጥሪየን አስተላልፋለሁ። ኑ! የከተማችንን ሌማት በጋራ እንሙላ እላለሁ።

# የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

**ስለከተማ ግብርና ምን ያህል ያውቃሉ?**

የከተማ ግብርና ልማትን በማስፋፋት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ በመፈናቀላቸዉ ተጎጂ የሆኑ አርሶ አደሮችን እና ቤተሰቦቻቸዉን ከደረሰባቸዉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ችግሮች ማላቀቅ እና በዘላቂነት ማቋቋም እንዲሁም የእንስሳት ጤና አገልግሎትን እና የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የኢንስፔክሽንና ሬጉላሪ አሰራርን በማሻሻል የህብረተሰቡን የበሽታ ተጋላጭነት መቀነስ እና አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ አርሶ አደርና ከተማ ግበርና ልማት ኮሚሽን ትኩረት ሰጥቶ የሚያከናወናቸው ተግባራት ናቸው። ሁሉን አሳታፊ የሆነ የከተማ ግብርና ተጠቃሚነት እንዲፈጠር ደግሞ አግባብነት ያለው የኮሙዩኒኬሽን ተግባቦትን መጠቀም መተኪያ የሌለው ጉዳይ ነው።

የከተማ ግብርና ማለት አነስተኛ በሆኑ ቦታዎች ላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የእንስሳት (የዶሮ፣ወተት፣ዓሣና ድለባ) የእፀዋት (አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት) ልማት በማካሄድ ማምረትና የተመረቱ ምርቶችን ማቀነባበር፣ በማከፋፈል ጨምሮ ምርቱን ለቤት ፍጆታ ከማዋል ባሻገር ለሽያጭ በማዋል ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንዲፈጥር ያደርጋል።

ኮሚሽኑ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ከግብ ለማድረስ እየሰራ ሲሆን እነርሱም የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን መልሶ ማቋቋም እና በቀጣይም አርሶ አደሩ ከከተማዋ ልማት ጋር አብሮ እንዲለማ ማድረግ፤ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በከተማው የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እና ለከተማዋ የሚቀርቡ የግብርና ምርትና ግብዓት ጥራት እና ሃይጅን ተጠብቆ መቅረቡን ማረጋገጥ ነው። ከዚህ የተነሳ የኮሚሽኑ የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬትም እነዚህን መሰረታዊ አጀንዳዎች ለማሳካት የመረጃ ጥራትና ተደራሽነት ማስፋት እና የተቀናጀ የቴክኖሎጅ አጠቃቀም ሥርዓትን ማሻሻል በዋናነት ትኩረት በማድረግ እየሰራ ይገኛል።

በመሆኑም የኮሚሽኑን መደበኛ ስራዎች እና ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታውን የዋጀ በተለያዩ የኮሙዩኒኬሽን አግባቦች ወቅቱን ጠብቆ ተዓማኒ የሆኑ መረጃዎችን ተደራሽ የማድረግ ስራ ይሰራል።

የከተማ ግብርና ጥቅም ለህብረተሰቡ በአነስተኛ ወጪ ትኩስ ጤናማና የተመጣጠነ የአትክልት ምግቦችን እንዲመገብ ያስችላል፤በዚህም ጤናው የተጠበቀ ማህበረሰብ እንዲፈጠር ያደርጋል፤የሴቶች ኢኮኖሚያዊ አቅም እንዲያድግና በራስ መተማመን እንዲጎለብት ያደርጋል፤ለሴቶች፣ ወጣቶችና አረጋውያን የስራ እድል እንዲፈጠር ያረጋል፤የመኖሪያ ግቢን እንዲሁም የአካባቢ ውበትን በመጠበቅ ሰዎች የእለት ተእለት ስራቸውን እና ውሎዋቸውን በተነቃቃ መንፈስ እንዲያሳልፉ ያስችላል፤የአረንጉዴ ሽፋንን ከፍ በማድረግ በከተማ የሚስተዋለውን ከፍተኛ የሙቀት መጠን እንዲቀንስ ጉልህ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላል፤በከተሞች የስራ አጥነትን ይቀንሳል፤በከተሞች የሚፈጠረውን የምግብ እጥረትና የዋጋ ውድነትን የቀንሳል፤የቤተሰብ ተጨማሪ የገቢ ምንጭን በማሳደግ የተሻለ ኑሮ እንዲኖራቸው ይረዳል።



## በከተማ ግብርና ከለውጡ በኋላ የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች

በከተማ ላይ የግብርና ስራ የማይታሰብ እና በሰፊ ቦታ ላይ ብቻ እንደሚሰራ ህብረተሰቡ በአመለካከት ታጥሮ የቆየ ነበረ። ይሁንና የከተማ ግብርና ስራ ዘርፍ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በከተማ ነዋሪ ህዝብ ላይ የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ ሰፊ ስራዎችን በመስራት በቤተሰብ ደረጃ በግቢና በጓሮ አትክልት ልማት፣ በተቋማት ክፍት ቦታዎች የግብርና ልማት ስራዎች እንዲከናወኑ በማድረግ እና የከተማ ነዋሪዎች በእንስሳት ሃብት ልማት ስራዎች/በዶሮ ልማት፣ በወተት ልማት…/ በስፋት እንዲሳተፉ በማድረግ የማስፋፋት ስራ በስፋት እየተሰራ ይገኛል፡ ፡ ቴክኖሎጅን ተጠቅሞ ከማምረት አንፃርም በጠባብ ቦታዎች ላይ ውጤታማ የሆኑ የግብርና ስራዎችን በማከናወን ምርትና ምርታማነት እንዲጨምርና በከተማው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ዘርፉ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲጫወት እየተደረገ ነው።

የግብርና ልማት በከተሞች ላይ አይቻልም የሚለው አመለካከት በተጠናከረ ስራ ሰርቶ በማሳየት እና በመቀየር ነዋሪውን በስፋት በማሳተፍ ውጤታማ እየሆነ መጥቷል። በሌላ መልኩ የከተማ ግብርና እጅግ በጣም አነስተኛ በሆኑ ቦታዎች ላይ ወይንም በቤት ግድግዳ፣ ጣሪና አጥር ላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የእንስሳት (የዶሮ፣ ወተት፣ ዓሣና ማድለብ) የእፀዋት (አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብት) ልማት በማካሄድ ማምረትና የተመረቱ ምርቶችን እሴት ጨምሮ በማቀነባበር እና በማከፋፈል ምርቱን ለቤት ፍጆታ ከማዋል ባሻገር ለሽያጭ በማዋል ተጨማሪ የገቢ ምንጭ በመፍጠር የቤተሰብን ኢኮኖሚ እንዲያሳድግ እየተደረገ ነው። ይህም እንዲሆን ኮሚሽኑ እጅግ በጣም በርካታ ሥራዎችን ሰርቷል፤ ስኬትም አስመዝግቧል።

## የተጠቃሚዎች ቁጥር ማሳደግ ተችሏል፤

የከተማ ግብርና ስራ አብዛኛው የከተማው ማህበረሰብ ትኩረት ሰጥቶ የማይሰራው የነበረ እና ከለውጡ ማግስት በኋላ ግን የመንግስትም አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ በመያዙ እና ሰፊ ስራ በመሰራቱ በርካታ የከተማው ማህበረሰብ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ እንዲሆን አስችሏል። በዚህም በ2012 በጀት ዓመት በከተማ ግብርና ስራ አጠቃላይ 116,264 ተሳታፊዎች (ተጠቃሚ) የነበሩ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 1,149,294 ተሳታፊ (ተጠቃሚ) ደረጃ ማድረስ ተችሏል፤
ቀደም ሲል ያልነበር ከለውጡ በኋላ ግን በመንግስትና በግል ተቋማት ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ባላቸው ክፍት ቦታዎች 2,667 ተቋማትን የተቀናጀና ዘመናዊ የግብርና ስራ ላይ በማስገባት እና እንዲያስፋፉ በማድረግ ለሰራተኞች ምርት በማቀረብ፣ ማእድ በማጋራት፣ ለአነስተኛ ደመወዝተኞች ተጨማሪ ገቢ መፍጠር እየተቻለ መጥቷል።

በአጠቃላይ በከተማ ግብርና ማለትም በእንስሳት እና እፅዋት ዘርፍ ልማት ነባር ተሳታፊ የሚሆኑ ማህበረሰብ ክፍሎች

| በጀት ዓመት | ነባር ተጠቃሚዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|
| | በእንስሳት ልማት ዘርፍ | በእፅዋት ልማት ዘርፍ | ድምር |
| 2012 | 37,671 | 78,593 | 116,264 |
| 2013 | 48,879 | 107,188 | 156,067 |
| 2014 | 38,569 | 380,498 | 419,067 |
| 2015 | 110,444 | 379,319 | 489,763 |
| 2016 | 215,636 | 506,431 | 722,067 |
| 2017 | 370,041 | 661,254 | 1,031,295 |

## ለበርካታ የከተማ ዜጎች የሥራ ዕድል በከተማ ግብርና ዘርፍ መፍጠር መቻሉ፤

የከተማዋ የስራ እድል ከመፍጠር እና ኢኮኖሚዋን ከማሳደግ አንፃር የከተማ ግብርና ዘርፍ ያለው ሚና የላቀ ሲሆን በዚህም ከለውጥ በፊት በ2011 በጀት ዓመት ለ1,672 ዜጎች የሥራ ዕድል የተፈጠረ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን የፈጠረው የስራ እድል በ2017 በጀት ዓመት ብቻ 26,312 ለሆኑ የከተማው ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር እና ተጠቃሚም ማድረግ ከመቻሉም ባሻገር በከተማ ግብርና ምርት ግብይት ላይ የድርሻውን ሚና በመጨታወት ሁለገብ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ እያደረገ ይገኛል።

| በጀት ዓመት | በከተማ ግብርና የተፈጠረ የሥራ እድል ተጠቃሚዎች ብዛት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| | በእንስሳት ልማት ዘርፍ | በእፅዋት ልማት ዘርፍ | ድምር | |
| 2011 | | | 1,672 | |
| 2012 | 3,071 | 12,488 | 15,559 | |
| 2013 | 4,874 | 8,409 | 13,283 | |
| 2014 | 3,687 | 6,088 | 9,775 | |
| 2015 | 13,425 | 6,996 | 20,421 | |
| 2016 | 12,338 | 5,850 | 18,188 | |
| 2017 | 18,864 | 7,448 | 26,312 | |
| 2018 | [illegible] | [illegible] | 13,740 | እስከ ታህሳስ 30/04/2018 ዓ.ም |
| | | | [illegible] | |







## የግብርና ምርት አቅርቦት ማሳደግ መቻሉ፤

የከተማ ግብርናን በማስፋፋት፣ በማጠናከር እና በማዘመን ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በከተማው የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ ሂደት ድርሻውን ከማሳደግ አንፃር በእንስሳት 30,302 ቶን ምርት እና በእጽዋት 19,008 ቶን ምርት በ2011 በጀት ዓመት በድምሩ 49,310 ቶን ምርት ይገኝ የነበረ አመታዊ ጠቅላላ ምርት መጠን በ2017 በጀት ዓመት በእንስሳት 194,748 ቶን ምርት እና በእጽዋት 85,658 ቶን ምርት በድምሩ በዓመት 280,406 ቶን ምርት ማድረስ ተችሏል። በከተማው በመኸር እና በመስኖ ልማት 7,165 ሄ/ር መሬት እየለማ ይገኛል። የከተማ ግብርና የኑሮ ወድነትን የማረጋገት ሚና እያደገ መጥቷል፤ የግብርና ምርትና ምርታማነት በማደጉ ለገበያ አቅርቦት አስተዋጽኦ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ለምሳሌ በ2011 በጀት ዓመት የእንቁላል ምርት 44,730,000 በቁጥር የነበረው በ2017 በጀት ዓመት ወደ 823,017,113 ሚሊዮን እንቁላል እንዲሁም በ2011 በጀት ዓመት 28,956,000 ሚሊዮን ሊትር ወተት የነበረው በ2017 በጀት ዓመት ወደ 71,048,867 ሚሊዮን ሊትር ወተት ምርት የማምረት አቅም ማሳደግ ተችሏል።

## በከተማ ግብርና ልማት በቤተሰብ ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግና ወደ ፋሚሊ ቢዝነስ ማሳደግ መቻሉ፤

በከተማ ግብርና በተለይም በእንስሳት ሃብት ልማት በቤተሰብ ፋጆታ ደረጃ አምስት ዶሮ ይዘው ወደ ስራ የገቡ ተጠቃሚዎችን ተከታታይነት ያለው የአቅም ግንባታ እና የግብዓትና ቴክኖሎጂ አቅርቦትንና ስርጭትን እንዲሁም ሙያዊ ድጋፎችን በማድረግ የዶሮ ቁጥራቸውን እስከ ሃምሳ እና ከዚያ በላይ እንዲያሳድጉ በማስቻል ወደ ፋሚሊ ቢዝነስ በማሻገር ከቤተሰብ ፍጆታ በተጨማሪ ምርታቸውን ለገበያ በማቅረብ በገቢ ማስገኛነት እንዲጠቀሙ አስችሏል።

| በከተማ ግብርና የተገኘ የሰብል ልማት ምርት | መለኪያ | በጀት ዓመት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 30/06/2018 |
| የመኸር ሰብል ምርት | በቶን | 8,097 | 8,654 | 4,451 | 29,885 | 14,195 | 18,699 | 18,621 |
| ከማሳ አትክልት ምርት | በቶን | 6,030 | 6,206 | 7,641 | 8,065 | 22,806 | 46,150 | 30,270 |
| ከጓሮ አትክልት ምርት | በቶን | 2,896 | 2,649 | 3,861 | 3,345 | 6,580 | 20,790 | 13,048 |
| ከእንጉዳይ ምርት | በቶን | 0 | 3 | 5 | 3 | 4 | 3 | 2 |
| ጠቅላላ ድምር | በቶን | 17,023 | 17,402 | 25,903 | 41,273 | 44,572 | 85,562 | 61,941 |

| የእንስሳት ልማት ምርት | መለኪያ | በጀት ዓመት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 30/06/2018 |
| የላም ወተት ምርት | በሊትር | 19,055,000 | 22,325,300 | 22,391,700 | 26,367,300 | 46,022,000 | 71,048,867 | 63,533,341 |
| የቀንድ ከብት ስጋ ምርት | በቶን | 11,673 | 14,171 | 20,736 | 30,390 | 29,909 | 69,930 | 15,068 |
| የዶሮ ስጋ ምርት | በቶን | 1,039 | 3,159 | 4,460 | 5,384 | 9,700 | 8,291 | 5,283 |
| እንቁላል ምርት | በቁጥር | 30,734,000 | 137,152,300 | 146,574,300 | 292,404,600 | 570,554,000 | 823,017,113 | 536,237,524 |
| ማር ምርት | [illegible] | 340,300 | 373,100 | 416,300 | 496,350 | 470,000 | 470,046 | 282,973 |
| የዓሳ ምርት | [illegible] | . | . | . | 1,250 | 7,000 | 9,414 | 8,133 |
| ጠቅላላ ድምር | በቶን | 48,925 | 50,101 | 55,559 | 78,890 | 127,298 | 194,748 | 116,895 |



## የከተማ ግብርና ስራ ገበያ ማረጋጋት ላይ ጉልህ ሚና እየተጫወተ መምጣት መቻሉ፤

አሁን ካለው የከተማዋ የህዝብ ቁጥር እድገት እና የከተማ ግብርና ምርት ፍላጎት መጨመር ጋር ተያይዞ ያለውን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ታሳቢ በማድረግ ነዋሪዎችን በስፋት በዘርፉ በማሳተፍ ደህንነቱ፣ ጤንነቱ የተጠበቀ ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ በ163 የቅዳሜና እሁድ የገበያ ቦታዎች ላይ አምራቾች ምርታቸውን እንዲያቀርቡ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፤ በዚህም ተጨባጭ ውጤት ማግኘት ተችሏል።

በሌላ መልኩ ኮሚሽኑ ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት በመነሳት ለገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርትና ግብዓት ጥራት እና ሃይጅን ተጠብቆ መቅረቡን በማረጋገጥ የህብረተሰቡን በሽታ ተጋላጭነት በመከላከል ጤናማና የበለጸገ አምራች ማህበረሰብ ለመፍጠር ሰፊ ስራዎችን ሰርቷል።

በአጠቃላይ በሌማት ትሩፋት ንቅናቄ ታግዞ የከተማ ግብርና ስራ በከተማው ባህል እየሆነ የመጣ ሲሆን ገበያን ከማረጋጋት ባሻገር በከተማዋ ሁለንተናዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከዓመት ዓመት እየጎላ መጥቷል።

## የሌማት ትሩፋት ስራ በከተማ ደረጃ ባህል እየሆነ መምጣቱና እና የስረዓተ ምግብ ማሻሻል መቻሉ፤

የከተማዋ የስራ እድል ከመፍጠር እና ኢኮኖሚዋን ከማሳደግ አንፃር የከተማ ግብርና ዘርፍ ያለው ሚና የላቀ ሲሆን በዚህም ከለውጥ በፊት በ2011 በጀት ዓመት ለ1,672 ዜጎች የሥራ ዕድል የተፈጠረ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን የፈጠረው የስራ እድል በ2017 በጀት ዓመት ብቻ 26,312 ለሆኑ የከተማው ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር እና ተጠቃሚም ማድረግ ከመቻሉም ባሻገር በከተማ ግብርና ምርት ግብይት ላይ የድርሻውን ሚና በመጨ‌ታወት ሁለገብ ተጠቃሚት እንዲረጋገጥ እያደረገ ይገኛል።



















## የሌማት ትሩፋት ስራ በከተማ ደረጃ ባህል እየሆነ መምጣቱና እና የስረዓተ ምግብ ማሻሻል መቻሉ፤

ከተማ አስተዳደሩ እንዲሁም ኮሚሽኑ ለሌማት ትሩፋት የከተማ ግብርና ልማት በሰጠው ልዩ ትኩረት ነዋሪዎችን በስፋት በማሳተፍ፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት፣ ግብዓትና ቴክኖሎጂ በማቅረብ፣ ሰፊ ስራ በማከናወኑ ከቤተሰብ ፍጆታ ባለፈ ተጨማሪ ገቢ ማስገኛ እንዲሆን አስችሏል።

የከተማ ነዋሪዉን የስራ ባህል እና አስተሳሰብ ለዉጥ በማምጣት ተሳታፊዎችን በማሳደግ በአረንጓዴ አሻራና በጓሮ አትክልት ያሳካነውን በዶሮ እርባታ፣ በወተትና በማር የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ግብ እውን በማድረግ ዘጎቻችንን የምግብ ፍላጎት በማሟላት ሌማታቸው የሚትረፈረፍና ለብዙ ወገኖቻችን የስራ እድል እንዲፈጠር ማድረግ ተችሏል። ለበርካታ ዜጎች ከደጃቸው በሚገኝ የግብርና ምርት ማዕዳቸውን የማሻሻል ብሎም ከራስ ፍጆታ አልፎ ለገበያ በማቅረብ ተጨማሪ ገቢ ማስገኘት ተችሏል።

በዚህም የከተማ ግብርና በሌማት ትሩፋት ንቅናቄ አማካኝነት በስፋት እና በጥልቀት በከተማዋ ማከናወን በመቻላችን አሁን በነዋሪዎች ዘንድ ባህል እየሆነ በመምጣቱ ከሸማችነት ወደ አምራችነት ከመሸጋገር ባሻገር ማህበራዊ ትስስሩን እያጠናከረ ይገኛል።



# የከተማውን አርሶ አደሮች በከተማ ግብርና በስፋት እንዲሰተፉ በማድረግ ፍትኃዊ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ መቻሉ፤

በከተማዋ በስድስት የማስፋፊያ ክ/ከተሞች የሚገኙ አርሶ አደሮችን ፍላጎትና ጥያቄያቸውን በመረዳት እና ትኩረት በመስጠት አመለካከታቸውን በማጎልበት በስፋት በይዞታቸው ላይ የከተማ ግብርና የሚያስፋፉበትን ምቹ ሁኔታ ማለትም የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት፣ ግብዓትና ቴክኖሎጂ በማቅረብ (የአፈር ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ ትራክተር፣ ቢቢኤም፣ የውሃ ፓምፕ .../ በማቅረብ በእፅዋት ልማት እና በእንስሳት ሃብት ልማት እንዲሰታፉ በማድረግ ብሎም ወደ ኢንቨስትመት እንዲሸጋገሩ በማመቻቸት ተጠቃሚነታቸውን የማረጋገጥና በከተማው የኢኮኖሚ እድገትና ልማት ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅ እንዲያበረክቱ የማድረግ ስራ ተሰርቷል።

በሌላ በኩል የልማት ተነሺ የሆኑ አርሶ አደሮችን ምንም ገቢ ለሌላቸውና መስራት ለማይችሉ የመሰረታዊ ፍጆታና የቤት ኪራይ በየወሩ በመደጎም፣ መስራት ለሚችሉና ገቢ ለሌላቸው ስልጠና በቴክኒክና ሙያ ተቋማት በመስጠት፣ የፋይናንስና የማሽነሪ እንዲሁም የቁሳቁስ ድጋፍ በመስጠት የሥራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፤ መስራት ለሚችሉና ገቢ ላላቸው ደግሞ ድጋፍ በማድረግ ከከተማዋ ልማት ጋር አብረው እንዲለሙ የማድረግ ሥራ በስፋት ተሰርቷል።

ከዚህ በተጨማሪ አርሶ አደር ለሆኑት መብት እንዲፈጠርላቸው ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ሰፊ ሥራ ተሰርቷል፤ እየተሰራም ይገኛል፡





## ማጠቃለያ

በአጠቃለይ ግብርና ከተማ ላይ አይቻልም የሚለው አመለካከት ተቀይሮ ባህል እየሆነ መምጣቱ እና በከተማው የሚካሄደው የከተማ ግብርና ስራ በአብዛኛው የከተማው ማህበረሰብ ተጠቃሚና ተሳታፊ ማድረግ መቻሉ፤ ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል መፍጠሩ፣ የቤተሰብ ገቢ እየተሻሻለ መምጣቱ፣ የምርት እድገትና አቅርቦቱ እያደገ መምጣቱ፤ የከተማ ግብርና ምርቶች የግብርና ምርት ዋጋ ላይ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ መምጣቱ፤ የግብዓትና የቴክኖሎጂ አቅርቦትና ተጠቃሚነት እያደገ መምጣቱ፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የግብርና ምርት ማዕከል እየሆኑ መምጣታቸው በዋናነት የሚጠቀሱ ለውጦች ናቸው።

በመሆኑም በከተማዋ ህብረተሰቡን በስፋት በከተማ ግብርና በማሳተፍ ውጤታማ የሆነ የከተማ ግብርና ልማት ኤክስቴንሽን በመተግበር፣ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ ጤንነቱ ደህንነቱ የተጠበቀ ምርት ለገበያ እንዲቀርብ በማስቻል፤ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንዲጠናከር ከማድረጋችንም በላይ አርሶ አደሮችን በተለይም የልማት ተነሺዎችን በማቋቋም እና በከተማ ግብርና ልማት ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ በማድረግ ኮሚሽኑ የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት እንዲወጣ የማስቻል ስራ ተሰርቷል።

# አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን

- የጽ/ቤት ኃላፊ
  - የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
  - ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት
  - ግዥና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
  - ዕቅድና በጀት ዳይሬክቶሬት
  - ኮመንኬሽን ዳይሬክቶሬት
  - አገልግሎት አሰጣጥ፣ክትትል፣ድጋፍ እና ምዘና ዳይሬክቶሬት
  - የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክቶሬት
  - የቅሬታና አቤቱታ አቀባበልና አፈታት ሕግ ምክር አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
  - የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
  - ICT ቡድን
- የአርሶ አደር ማቋቋም ልማት ዘርፍ
  - የአርሶ አደር ማቋቋም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ሰርተፍኬሽን፣ ኢንስፔክሽን፣ኳራንቲንና ሬጉላቶሪ ዘርፍ
  - ሰርተፍኬሽን፣ ኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ ዳይሬክቶሬት
- የከተማ ግብርና ልማት ዘርፍ
  - የእንስሳት ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት
  - የእጽዋት ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት
  - የእንስሳት ልማት እና ልኅቀት ማዕከል
  - የከተማ ግብርና ሰርቶ ማሳያና ግብዓት ብዜት ማዕከል















